# ከወጣቶች ለወጣቶች

# የትግል ጥሪ

የዛሬውን አያድርገውና ሐገራችን ኢትዮጵያ የገናና ታሪክ ባለቤት ለመሆን የበቃችው በበሳልና በብልህ ዜጎቿ የሰከነ አመራር ስጪነት ብቻም ሳይሆን በወቅቱ ሐላፊነትን ለመሸከም የቻሉ ብቁ የሆኑ ዜጎች ለማፍራት በመቻሏም ጭምር እንደነበር ታሪካችን ምስክር ነው።

እኛ የአሁኑ ዘመን ትውልድ ወጣቶች በሐገራችን ላይ የመጣው መርገምት ያጎሳቆለን፣ ኑሮ የበደለን፣ ያልታደልን ፍጡሮች ብንሆንም የሰው ምርት አልቀ በግርዱ ዘመን አይደለምና የደረስነው ህዝባችን ነጻነቱን ሲቀማ፣ መብቱ ሲደፈር፣ ክብሩ ሲዋረድ እዳር ቆመን የምንመለከትበት ምክንያት የለም። ወቅቱ ለነፃነታችንና ለመብታችን ባላንጣ የሆነውን እርኩስ ኃይል ፊት ለፊት ተጋፍጠን፣ በትግላችን ደቁስን ማንነታችንን የምናስመሰክርብት ወቅት እንጂ እንደግመል ሽንት ወደኋላ የምንፈተለክበት ሰዓት ጨርሶ ሊሆን አይችልም።

በኢትዮጵያ የታሪክ ማሕደር ታላቅ ተብሎ ሊሰየም በሚችለው የወጣቶች ንቅናቄ ዘመን ኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ጋሼ ሐይሉ ገብረዮሐንስ "ያስብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ ሁኔታው ስጠጥር፣ ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር" ማለታችው በነፃነትና መብትህ ላይ ብቻም ሳይሆን በነገ ተስፋህ ላይ ለዘመተ ባላጋራህ የሽንበቆ እግር ሆነህ አትቁም ማለታችው ይመስለናል። እኛ ወጣቶች ለመብታችን ካልታገልን ተወደደም ተጠላ ጭቆናን በዝምታ እንደተቀበልን ተደርጎ መወሰዱ የማይቀር ነው። ከምንግዜውም በላይ እኛን ወጣቶች ዛሬ ሁለት አበይት ጉዳዮች በጉልህ ያሳስቡናል እነዚህም ሐገራችን ያለችበት አሳሳቢ ሁኔታና የኛ የተተኪው ትውልድ የወደፊት ተስፋ ምን ሊሆን ይችላል? የሚሉት ናችው። በሐገራችን የተፈራረቁት አምባገነን ገዥዎች ለወጣቱ ተስፋና የተሻለ ነገር ሳይሆን የሚያቀርቡልን በጠላትነት ፈርጀው በሽብርና በጥቃት ያስተናግዱናል።

በዚህም ብቻ ሳያበቃ በአልባሌ ልምዶችና በጎጂ ባህሎች ያጥለቀልቁናል። የወያኔ መሪዎች ለኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ደዴሳን፣ ሁርሶን ሸዋሮቢትን ዝዋይን የመሳሰሉ እስር ቤቶችን ሲያስፋ እንጂ የሥልጠና የምርምር ተቃም ሲያድሱና ሲገነቡ ለማየት አልታደልንም። ባደባባይ ያለፍትህ የሚገደለው ወጣት ባንክ ሲዘርፍ ተገኘ፣ወንጀል ሲሰራ ተያዘ የሚሉ የሀሰት ምክንያቶች በመስጠት ያለሐጢያቱ የሀሰት ስም በመለቅለቅ ዳግም ይገሉታል። የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ከሚፈራበት የትምህርት ተቋም ድረስ በመግባት የአማራ ህንጻ የኦሮሞ ህንጻ...ወዘተ  እያሉ የትምህርት ሥረዓቱን ከጠባብ የፖለቲካ ግብ ጋር በማያያዝ በነገ ተስፋችን ላይ ዘምተው የልዩነት ግድግዳ ባሳፋሪ መልክ ይገነባሉ። አላማው ደግሞ በጎሰኝነት ናወዝን ከእህቶቻችንና ከወንድሞቻችን ጋር እየተናቸፍን የምንኖርበት ሲኦል

ለመፍጠር መሆኑ  አያጠያይቅም። በዚህም ሳቢያ ብሔራዊ ስሜታችን እየደበዘዘ ይሔዳል ብሔራዊ ስሜት ከሌለን አገር አለን ማለት ጨርሶ የሚታሰብ አይሆንም።

ሰሞኑን ወያኔዎች የኢትዮጵያ ወጣቶች “ብሔራዊ የወጣቶች ፌዴሬሽን” በሚል ስም ተደራጅተው ለእድገትና ለልማት መዘጋጀታችውን አበሰሩ ይሉናል...መቼም ወግ ላፍ አይቀርና ። ዛሬ ሥርዓቱ በፈጠረው ችግር በሀገሪቱ የወጣት ሥራ ፈትና ተጧሪ ካፍ እስከገደፉ ሞልቶና ተትረፍርፎ በሚታይበት፣ ሥራ የማግኘት እድል በፖለቲካ ታማኝነት ብቻ በሆነባት ሐገርና ወያኔ የፖለቲካ ሥልጣኑንና ወታደራዊ ሐይሉን ተጠቅሞ የሀገሪቷን ሀብት እያጋበሰ በሚዘርፍበት ሁኔታ ልማትና እድገት የሚሉት ቃሎች ለእኛ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ተራ ማጭበርበሪያ ካልሆኑ በስተቀር ትርጉም የሚሰጡን አይደለም። ለእኛማ ወያኔ ከመጀመሪያው ጀምሮ  ያዘጋጇልን ደደሳን፣ ሁርሶን፣ሽዋሮቢትንና የመሳሰሉትን የማጎሪያ ቦታዎች  መሆኑን የተረዳን ስለሆነ በዚህ የምንደናገር አይደለም። ለዚህም ነው ባሁኑ ወቅት እኛ ወጣቶች ተሰባስበንና ተደራጅተን ከመታገል ውጪ ሌላ ምርጫ የሌለን። አምባገነንነት ካልተገታ የአገር ሰላም ሆነ የሕዝብ ሕልውናና አንድነት ዋስትና አያገኝም። በአሁኑ ውቅት በኢትዮጵያ ሥልጣን የጨበጡት ግለሰቦች የአገራችውን ሀብት እየተቀራመቱ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ፣ሕዝባችንን የሚረግጡና የሚበድሉ፣ለባዕድ ጥቅም የተገዙ ግለሰቦች ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ብሔራዊ  ስሜታችውን አሽቀንጥረው የጣሉ ፣ የራሳችውን ባህል ፣ ወግ ፣ ታሪክና ሕዝብ አምርረው የሚጠሉ ከራሳቸውና ሥልጣን ላይ ካስቀመጧቸው መንግሥታት ጥቅም ውጪ ሌላ ምንም የማይታያቸው ናችው። ታዲያ የሐገራችን ህልውና ከመቼውም በላይ ለከፋ አደጋ ተጋልጠ ባለበት በአሁኑ ወቅት በተለይ የኛ ወጣቶች ግዴታና ድርሻ ምን መሆን አለብት ብለን ራሳችንን መጠያቅና ብሎም መልስ ለመስጠት መሞከር ሐገራዊ ግዴታንና ኃላፊነትን ለመወጣት የመጀመሪያው ርምጃ ነው። ጭቆናና በደልን በመታገል በኩል የታላላቅ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን አኩሪ ገድል ለዛሬው ትግላችን ትልቅ የትምህርት ማእከል ሆኖ ያገለግለናል።

ሀገራችን ከኋላቀር ሥርዓትና ከብልሹ ገዠዎች አገዛዝ ተላቅቃ፣ ድህነትን አሽንቀጥራ ጥላ በልማት ጎዳና እንድትራመድ፥ ደሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን፣ ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን ባጠቃላይም ተጨባጭ ለውጥ በሐገራችን እንዲመጣ ጽኑ እምነት የነበራቸውና  ይህንንም ማድረግ ይቻላል ብለው አምነው ለሕዝባዊ ትግሉ ሕይወታቸውን መስዋዕት በማደረግ ሲታገሉ የነበሩትን ጀግኖች ወጣቶች ታሪክ ስናጠናና  በማይታበል ደረጃ ዛሬም ጭምር ግንባራችውን ሳያጥፉ መሥዋዕትነትን በመክፈል እያስመሰከሩ ያሉ መሆናችውን ስንመለከት ጀግና የሚያፈራው ጀግናን ነውና እኛም ወጣቶች አንገታችንን ቀና አድርገን የታላላቅ ወንድሞቻችንን ጥሪ ተቀብለን ዛሬም እንደ ትናንቱ ለሐገራችን ለህዝባችን ነፃነት መታገል ብሔራዊ ግዳጃችን ብቻም ሳይሆን ታላቅ ክብርም ጭምር መሆኑን እንገነዘባለን። ከፊታችን ለሚጠብቀንና ሐገራችን እያሰማችን ላለው ሀገር አድን ጥሪ መልስ ለመስጠት እኛ የኢትዮጵያ ወጣቶች  ከሐገር ቤት እስከ ውጪው አለም ድረስ የተቀናጀና የተቀነባበረ የትግል እንቅስቃሴ ለማድረግ ፍላጎቱና ምኞቱ አለን። በኅብረትና በጽናት ከታገልንም የ ሕዝባችንን ሮሮ ማዳመጣችን ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ ለውጥም ለማምጣት የሚቻል መሆኑን በእርግጠኛነት መናገር እንችላለን። ዛሬ በድቅድቅ ጨለማ

ውስጥ እንዳለ ብልጭ ብልጭ እንደሚል ኮኮብ ብንመስልም በርግጠኝነት ነገ ከፀሐይ ደምቀን ከአሸዋ በርከትን የምንታይበት ጊዜ እንደሚመጣ ሙሉ እምነት በመያዝ ነው።

እድሜ አገራችንን የውጭ ጠላትን በመከላከል ላቀይዋት ለጥንት አባቶቻችንና እናቶቻችን ይሁንና፤ በኢህአፓ፡ በኢህአወሌ፡በኢትህድ፡በጭዋማ፡በኢላማ ተስልፈው ክብር ህይወታችውን ለሐገራችው አሳልፈው ለሰጡ ታጋዮች ምስጋና ይድረስና እኛም ዛሬ እንደትናቱ የትግል ችቦ ለማቀጣጠል ተዘጋጅተናል። ለኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ለትግል እንነሳ የሚል ጥሪ እናቀርባልን

እንዘጋጅ የዛሬው ቃጭል ጥሪ የነገ ትልቅ ደወል ይሆናል!!

የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሐገር አድን ጥሪ እንዘጋጅ!!

*የወገኖቻችን ሰቃይና መከራ ያንገበገበን ወጣቶች*